

# Home Connection

**ተማሪዎችን ተገቢ ካልሆነ መነካት መጠበቅ**

ውድ ወላጅ ወይም አሳዳጊ:-

ተማሪዎች በተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢ ስለሆነ እና ተገቢ ስላልሆነ መነካት ሲማሩ ቆይተዋል። ምንም እንኳን ይህ በጣም አስቸጋሪ ርዕስ ቢሆንም ውይይቱ ለልጆቻችን ደህንነት አስፈላጊ ነው። እንደ CDC ዘገባ መሰረት፣ (https://www.cdc.gov/violenceprevention/childsexualabuse/fastfact.html) ከ4 ልጃገረዶች አንዷ እና ከ13 ወንድ ልጆች አንዱ የወሲባዊ ጥቃት ሰለባዎች ናቸው። በሚያሳዝን ሁኔታ፣ አብዛኛዎቹ ጥቃት አድራሾች የማይታወቁ ሰዎች ሳይሆኑ፤ ልጁ/ልጅቱ የሚያውቋቸው ሰዎች ናቸው። ዘመዶች፣ ጓደኞች ወይም ተንከባካቢዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

ልጆች "የመንካትን ደንብ" ተምረዋል:- ማንም ሰው እንዲነካችሁ በማትፈልጉት መንገድ ወይም ብልታችሁ አካባቢ - ንጽህናን ለመጠበቅ ካልሆነ በስተቀር - ሊነካችሁ መብት የለውም።

ልጆች ተገቢ ባልሆነ መንገድ እንደተነኩ ከተሰማቸው እምቢ የማለት ሃይል እንዳላቸው ሊሰማቸው ይገባል። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ያሉ ልጆች እምቢ እንዲሉ፣ ከቻሉ እንዲያመልጡ እና የሆነውን ለአንድ ሰው እንዲናገሩ አበረታተናል። ተገቢ ያልሆነ ንክኪ ወይም ጾታዊ ጥቃትን የሚገልፁ ልጆች የእርስዎን ድጋፍ ይፈልጋሉ። እንዲህ ልትሏቸው ይችላሉ፣ "ስለተፈጠረው ነገር ልትነግሩኝ በጣም ከባድ እንደሆነባችሁ አውቃለሁ።" ይህ የአንተ/የአንች ጥፋት እንዳልሆነ እንድታውቅ/ቂ እፈልጋለሁ። እኔ እንክብካቤ ላደርግልህና/ሽና ልረዳህ/ሽ ነው።" ለልጁ/ልጅቱ መናገር ትክክለኛ ነገር መሆኑን ያረጋግጡላቸው።

በደል የተፈፀመበት ወይም ተገቢ ባልሆነ መንገድ የተነካ/ች ልጅ ካወቁ፣ የፌርፋክስ ካውንቲ የህፃናት ጥበቃ አገልግሎት የቀጥታ የስልክ ቁጥርን (703) 324-7400 በመደወል ያነጋግሩ። በማንኛውም ጊዜ፣ ቀን ወይም ማታ መደወል ይችላሉ። በህጻናት ጥበቃ አገልግሎት ውስጥ ያሉ ማህበራዊ ሰራተኞች ጥቃት የደረሰባቸውን ልጆች ለመርዳት የሰለጠኑ ናቸው።

ልጅዎ ስለዚህ ርዕስ እነሱ ስላላቸው ማንኛውም ጥያቄ እንዲያናግሩዎት ያበረታቷቸው።

አመሰግናለሁ፣

የልጅዎ አስተማሪ